የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የሳምንታዊ መረጃ ማሰራጫ

# ሳምንታዊ የቢዝነስ መረጃዎች

(ሚያዝያ 14- 21/2016 ዓ.ም)
April 22- 29/2024

በኮርፖሬት ኮሙኒኬሽንና ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

## 1. በኢትዮጵያ የሚገኝ አንድ ቄራ ለመጀመሪያ ጊዜ የግመል ስጋ ወደ ሣውዲ አረቢያ መላክ ጀምሪያለሁ አለ

በኢትዮጵያ የሚገኝ አንድ ቄራ ለመጀመሪያ ጊዜ የግመል ስጋ ወደ ሣውዲ አረቢያ መላክ ጀምሪያለሁ አለ፡፡

ቄራው በወር በአማካይ እስከ ስልሣ ሺህ ኪሎ ግራም የግመል ስጋ ሣውዲ አረቢያ እየላከ እንደሚገኝ ሠምተናል፡፡

*Sheger Radio* **ሚያዝያ 16፣2016**

https://www.shegerfm.com/post/%E1%88%9A%E1%8B%AB%E1%8B%9D%E1%8B%AB-16-2016-%E1%89%A0%E1%8A%A2%E1%89%B5%E1%8B%AE%E1%8C%B5%E1%8B%AB%E1%8B%A8%E1%88%9A%E1%8C%88%E1%8A%9D-%E1%8A%A0%E1%8A%95%E1%8B%B5-%E1%89%84%E1%88%AB-%E1%88%88%E1%88%98%E1%8C%80%E1%88%98%E1%88%AA%E1%8B%AB-%E1%8C%8A%E1%8B%9C-%E1%8B%A8%E1%8C%8D%E1%88%98%E1%88%8D-%E1%88%B5%E1%8C%8B-%E1%8B%88%E1%8B%B0-%E1%88%A3%E1%8B%8D%E1%8B%B2-%E1%8A%A0%E1%88%A8%E1%89%A2%E1%8B%AB-%E1%88%98%E1%88%8B%E1%8A%AD-%E1%8C%80%E1%88%9D%E1%88%AA%E1%8B%AB%E1%88%88%E1%88%81-%E1%8A%A0%E1%88%88

## 2. በኢትዮጵያ ተገማች ያልሆነ የታክስ አስተዳደር እንዲስተካከል ተጠየቀ

በኢትዮጵያ የሚገኘው የአውሮፓ የንግድ ምክር ቤት በኢትዮጵያ የግብር አስተዳደር ላይ ያተኮረ የፖሊሲ ሰነድ ሚያዝያ 17 ቀን 2016 ዓ.ም. ይፋ አድርጓል፡፡

***Reporter: April 28, 2024***

በመድረኩ የተገኙት በኢትዮጵያ የአውሮፓ ኅብረት አምባሳደር ሮላንድ ኮቢያ፣ ኢትዮጵያ ከአውሮፓ ኅብረት በጣም ምቹ የሚባል፣ የንግድ ዕድል እያገኘች ቢሆንም፣ በኢትዮጵያ ያለው የታክስ አሠራር ተለዋዋጭና ሊገመት የማይችል ለኢንቨስተሮች የማይመች ስለመሆኑ አንስተዋል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/129031/

## 3. ከአንድ ሚሊዮን በላይ አርሶ አደሮች የሰብል መድን ዋስትና እንዲገቡ ሊደረግ ነው

በአማራ፣ በኦሮሚያና በትግራይ ክልሎች ከአንድ ሚሊዮን በላይ አርሶ አደሮች የሰብል መድን ዋስትና እንዲገቡ ለማድረግ ቅድመ ዝግጅት ማጠናቀቁን ፑል አድቫይዘር የሚባል ተቋም አስታወቀ፡፡

***Reporter: April 28, 2024***

ለአነስተኛ አርሶ አደሮች ተመጣጣኝ የመድን ሽፋን ለመስጠት ‹‹ኢንፑት ቫውቸር ሲስተም›› (IVS) የተሰኘ የመገበያያ ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን፣ አርሶ አደሮች ማዳበሪያ ሲገዙ የሰብል መድን ዋስትና አብረው እንዲገቡ በማድረግ ተግባራዊ የሚደረግ መሆኑን ተቋሙ ሐሙስ ሚያዝያ 17 ቀን 2016 ዓ.ም. አስታውቋል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/129008/

## 4. ብሔራዊ የኢ-ኮሜርስ ስትራቴጂ መንግስት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የሚያስፈጽመው ነው - ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ የዲጅታል ኢትዮጵያ ስትራቴጂ አካል የሆነው ብሔራዊ የኢ-ኮሜርስ ስትራቴጂ ረቂቅ ላይ የሚደረግ ውይይትን አስጀምረዋል፡፡

**ኢዜአ; ሚያዚያ 21/2016**

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ባሰፈሩት መልዕክት የዲጅታል ኢትዮጵያ ስትራቴጂ አካል የሆነው ብሔራዊ የኢ-ኮሜርስ ስትራቴጂ ረቂቅ ላይ የሚደረግ ውይይት ዛሬ በይፋ አስጀምረናል ብለዋል፡፡

**https://www.ena.et/web/amh/w/amh_4367213**

## 5. በአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት አለ የተባለው የውስጥ ችግር በውጭ ኦዲተሮች ሊመረመር ነው

በአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ውስጥ ታይተዋል የተባሉ ግድፈቶች በውጭ ኦዲተሮች ምርመራ እንዲደረግ የተወሰነውን ውሳኔ ለማስፈጸም ለምርመራው የሚመረጠው የውጭ ኦዲተር ውጤቱን በአንድ ወር አጠናቅቆ የሚያቀርብ መሆኑ ተጠቆመ፡፡

***Reporter: April 28, 2024***

ንግድ ምክር ቤቱ በቦርድ አባላት ጭምር በቀረበ አቤቱታ መሠረት የታዩ ግድፈቶችን ለመመርመር ለውጭ ኦዲተሮች ጥሪ የተላለፈ ሲሆን፣ የኦዲተር መረጣው በቀጣይ ሁለት ሳምንታት ይጠናቀቃል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ በንግድ ምክር ቤቱ አሉ የተባሉ ችግሮችን ለማስመርመር በንግድ ምክር ቤቱ ቦርድ የተሰየመው አጣሪ ኮሚቴ የኦዲት ሥራውን የሚመረምሩ ኦዲተሮች በጨረታ እንዲመረጡ በመወሰኑ፣ በዚሁ መሠረት ለተጫራቾች ጥሪ ተላልፏል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/129078/

## 6. የጥሬ ቡና ወጪ ንግድ ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት መደረጉ የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን ሥጋት ውስጥ ከቷል

ከዚህ በፊት ለውጭ ባለሀብቶች ዝግ ተደርጎ የነበረው የጥሬ ቡና ወጪ ንግድ የገበያ ሁኔታ ሳይስተካከል ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት መደረጉ፣ የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን ከገበያ ሊያስወጣ እንደሚችል ሥጋት እንዳለ ተነገረ፡፡

***Reporter: April 28, 2024***

በወጪና በገቢ ንግድ፣ እንዲሁም በጅምላና በችርቻሮ ንግድ የውጭ ባለሀብቶች እንዲገቡ ሲደረግ የገበያ ውድድርን ከመፍጠር አኳያ መልካም ጎን ቢኖረውም፣ መመርያው ገደቦችን ባለማስቀመጡ የአገር ውስጥ ቡና ላኪዎችን ከገበያ ሊያስወጣ እንደሚችል የቡና ላኪዎች ማኅበር ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ግዛት ወርቁ ለሪፖርተር ገልጸዋል፡፡

**https://www.ethiopianreporter.com/128916/**

### 7. ስምምነት ሊደረስበት ያልቻለው የኢትዮጵያና የአይኤምኤፍ ድርድር

ኢትዮጵያ የገጠማትን ከፍተኛ የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት ለማስተካከል በፅኑ የሚያስፈልጋትን የውጭ ብድር ወይም የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ለዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም (አይኤምኤፍ) እና ለፓሪስ ክለብ አበዳሪ አገሮች ጥያቄ አቅርባ ድርድር ከጀመረች ከሁለት ዓመት በላይ ቢቆጠሩም አሁንም መንገዶቹ አልጋ በአልጋ ሊሆኑላት አልቻሉም።

***Reporter April 24, 2024***

ኢትዮጵያ ከገጠማት የውጭ ምንዛሪ አጣብቂኝ ለመውጣት የዓለም አቀፉን የገንዘብ ተቋም ጠቀም ያለ ብድር ማግኘት የምትሻ ቢሆንም፣ በአሁኑ ወቅት ያለባት አጠቃላይ የውጭ ዕዳ መጠን ተጨማሪ የውጭ ብድር ለማግኘት የሚያስችል አለመሆኑ ፍላጎቷን ለመፈጸም አዳጋች አድርጎባታል።

https://www.ethiopianreporter.com/128989/

## በውጭ ቋንቋዎችና ከውጭ ሚዲያዎች

### 1. Wingu Africa becomes Ethiopia's first certified data center

Wingu Africa Group Limited, a leading data center provider in Ethiopia, has achieved a significant milestone by becoming the first in the country to meet international standards, with an investment of $50 million.

**Capital news paper April 22, 2024**

The company, which established a data center in Addis Ababa's ICT Park a year ago, announced that it has been awarded a Tier III quality certification by the Uptime Institute. The Uptime Institute is a global authority on digital infrastructure that evaluates data centers worldwide, similar to the International Organization for Standardization (ISO).

https://www.capitalethiopia.com/2024/04/22/wingu-africa-becomes-ethiopias-first-certified-data-center/

### 2. Agoa to be expanded to all of Africa and extended to 2041

The US Congress has put forward proposals that would see the African Growth and Opportunity Act (Agoa) extended to 2041.

Senators Chris Coons of Delaware and James Risch of Idaho last week introduced the bipartisan Agoa Renewal and Improvement Act of 2024, which would see Agoa cover 54 African countries.

**THEEAST AFRICAN: APRIL 28 2024**

The extension is expected to integrate Agoa with the African Continental Free Trade Agreement (AfCFTA) to support the development of intra-African supply chains. Enacted in 2000, Agoa is due to expire next year.

https://www.theeastafrican.co.ke/tea/business/agoa-to-be-expanded-to-all-of-africa-and-extended-to-2041--4605446

### 3. We've lifted barriers to foreign investment, Somalia PM Hamza Barre says

Somalia has removed a number of investment screening regimes that barred deployment of capital, giving foreigners the green light to wholly own their investments, repatriate capital and enjoy full protection in the country.

**THEEAST AFRICAN: APRIL 25 2024**

Somalia Prime Minister Hamza Abdi Barre said trade and investment restrictions arising from foreign investment regimes, cause output losses of about two per cent, hence Somalia's decision to enact the Investments and Investors Protection Law, 2023, to attract foreign capital.

https://www.theeastafrican.co.ke/tea/news/east-africa/we-ve-lifted-barriers-to-foreign-investment-somalia-pm-says-4602866

### 4. Iran seeks mutually beneficial cooperation with Africa: president

Iran's President Ebrahim Raisi said on Friday that his country sought to expand cooperation with African states.

Raisi made the remarks at the second International Economic Conference of Iran and Africa held in the Iranian capital Tehran, which was attended by high-ranking officials of different African countries, according to a statement published by the president's office.

**CGTN: APRIL 27 2024**

He said that Iran's leaders always highlight the necessity to enhance cooperation with African countries, adding the two sides should acquire greater knowledge of each other's capacities.

https://newsaf.cgtn.com/news/2024-04-27/Iran-seeks-mutually-beneficial-cooperation-with-Africa-president-1t7KOfq9RzW/p.html

### 5. Advantages of providing foreign companies wholesale, retail trade

The government of Ethiopia recently introduced a new regulation and rules which allow foreign companies to engage in whole sale and retail trade in the country following Prime Minister Abiy Ahmed's green light to do so.

**Ethiopian herald April 28, 2024**

Sectors previously deserved to the local business men will be opened to the foreigners step by step from now on and the scheme is expected to improve the trade and transaction system of the country. The regulation also opens the door to foreign business men to engage in import and export trade.

https://press.et/herald/?p=94815